abookmedwinchdotpress.com



እዲተር ወይም በርዱ በሚሰይማቸው የውጭ እዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ።

## አንቀጽ 20. መብትና ግዴታን ስለ ማስተላለፍ።

የቀድመው ኪ.ቤ.እ.ድ.ድርጅት የሐረር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለድርጅቱ ተላልፈዋል።

## አንቀጽ 21. ስለ ትርፍ አከፋፈል

የድርጅቱን የተመረመረና የተጣራ ትርፍ አከፋፈልን በሚመለከት በርዱ ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ውሳኔ ያቀርባል።

## አንቀጽ 22. የኃላፊነት ወሰን

ድርጅቱ በዕዳ ተጠያቂ የሚሆነው ጠቅላላ ያለው ንብረት እስከሚሸፍነው ድረስ ብቻ ነው።

## አንቀጽ 23. ተፈጻሚነት የሌላቸው ሕጎች

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም የክልሉ ሕግ፣ ደንብ ወይም መመሪያ በዚህ አዋጅ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

## አንቀጽ 24. ደንብ የማውጣት ሥልጣን

የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉትን ደንቦችና መመሪያዎች የማውጣት ሥልጣን ይኖረዋል።

## አንቀጽ 25. የመተባበር ግዴታ

ይህን አዋጅ በሥራ ላይ ለማዋል ማንኛውም ጉዳዩ የሚመለከተው በክልሉ የሚገኝ የመንግሥት መሥሪያ ቤት፣ የፖለቲካ ድርጅት ወይም ግለሰብ የመተባበር ግዴታ አለበት።

## አንቀጽ 26. አዋጁን ስለማሻሻል ወይም ስለ መሻር

ይህንን አዋጅ የማሻሻል ወይም የመሠረዝ ሥልጣን የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ነው።

## አንቀጽ 27 አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በሐረሪ ነጋሪ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

ሐረር የካቲት 25 ቀን 1991 ዓ.ም

አብዱላሂ ኢድሪስ

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ

መንግሥት ፕሬዝዳንት